# የኢትዮጵያ የመሬት አስተዳደር ባለሞያዎች ማህበር

**የመመሥረቻ ጽሁፍና**

**የመተዳደሪያ ደንብ**

**2001 ዓ.ም**

**ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ**

## መግቢያ

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ያለን የመሬት ባለሙያዎች በአንድ የጋራ መድረክ ላይ ተሰባስበን ሃሳባችንንና እውቀታችን ስራ ላይ እንድናውል ለማስቻል፤

ይህን ዕውቀታችንና የምርምር ውጤታችን ለመስል ባለሞያዎችና ለህብረተሰቡ የምናስተላልፍበት መድረክ በማስፈለጉ፤

ዕውቀታችንና ችሎታችን መሰረት በማድረግ የፖሊስና ህግ ነክ ምክርና ድጋፍ ለመንግስት እንድንሰጥ ለማስቻል፤

የኢትዮጵያ የመሬት አስተዳደርን ለማገዝ ከዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ አስፈላጊ ልምዶችን ለመቅሰምና የእኛንም ልምድ ማካፈል በማስፈለጉ፤እና

በአንድ ማህበር ሥር በመሰባሰብ ሙያዊ ክህሎታቸንን የምናዳብርበት ሁኔታ በመፍጠር ከዚህ ተጠቃሚ እንድንሆን ለማስቻል ይህ የኢትዮጵያ የመሬት አስተዳደር ባለሞያዎች ማህበር የመተዳደሪያ ደንብ ወጥቷል፡፡

### አንቀጽ 1. ስለማህበሩ መቋቋም

ይህ የኢትዮጵያ የመሬት አስተዳደር ባለሞያዎች ማህበር በ1952 የፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 404 እና ተከታዬቹ ድንጋጌዎች እንዲሁም በበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 መሰረት ተkቁሟል፡፡

### አንቀጽ 2. ትርጓሜ

1. “መሬት” ማለት ሁሉም ዓይነት ተለይተው የተቀመጡ የማይነቀሳቀሱ ንብረቶች ማለት ሲሆን ለምሳሌ ማሳ፣ ሕንጻ፣ አጥርና ከመሬት ላይም ሆነ ውስጥ ለkሚ አገልግሎት የተገነቡ ስራዎች፣ ዛፎችና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡
2. “የመሬት አስተዳደር” ማለት የመሬት አጠቃቀም ስልቶችን ተግባር ላይ ለማዋል ሲባል የሚከናወን ስለመሬት ይዞታ፣ዋጋ፣ ጠቀሜታና ለመሳሰሉት መረጃዎች መወሰን፣መመዝገብና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ማሰራጨት ማለት ነው፡፡

3. “የመሬት አስተዳደር ባለሞያ” ማለት ከመሬት አስተዳደር ጋር የተገናኘ ትምህርት ወይም ልምድ ያለው ማለት ነው፡፡
4. "ማህበር" ማለት የኢትዮጵያ የመሬት አስተዳደር ባለሞያዎች ማህበር ማለት ነው፡፡
5. "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም የህጋዊ የሰውነት ማረጋገጫ የተሰጠው ድርጅት ነው፡፡
6. "አባል" ማለት ማንኛወም የተፈጥሮ ወይም የህጋዊ የኢትዮጵያ የመሬት አስተዳደር ባለሞያዎች ማህበር መስራች በመሆን የተመዘገበ ወይም ማህበሩ ከተቋቋመ በኋላ የማህበሩ አባል ለመሆን የሚመዘገብ ማንኛውም ሰው ነው፡፡
7. "ተባባሪ አባል" ማለት በማህበሩ ውስጥ የመምረጥና የመመረጥ መብት የሌለው የማህበሩን ዓላማዎች ደግፎ የሚያግዝ አባል ማለት ነው፡፡
8. “ተማሪ” ማለት በአንቀጽ 21 (ሀ) በተጠቀሱት የትምህርት ዘርፎች በአንዱ በኮሌጅ ወይም ዩኒቨርስቲ በመማር ላይ ያለ ነው፡፡
9. "ጠቅላላ ጉባኤ" ማለት የዚህ ማህበር አባላት የሆነና ወደፊት ማህበሩ ቅርንጫፎችን ሲከፍት ቅርንጫፎቹን የሚወክሉት የሚገኙበት ጉባኤ እና የስልጣን አካል ነው፡፡
10. "ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ" ማለት በጠቅላላ ጉባኤው የተመረጡ አባላትን ያቀፈ የማህበሩ ሥራ አስፈፃሚ /አመራር/ አካል ነው፡፡
11. "ቅርንጫፍ" ማለት በማንኛውም ደረጃና በየትኛውም ቦታ የሚገኝ የማህበሩ ቅርንጫፍ ማለት ነው

**አንቀጽ 3 የማህበሩ መጠሪያ**

ማህበሩ "የኢትዮጵያ የመሬት አስተዳደር ባለሞያዎች ማህበር" ማህበር ተብሎ ይጠራል፡፡

**አንቀጽ 4 የማህበሩ አድራሻና ጽ/ቤቶች**

1. የማህበሩ የፖስታና ሌሎች አድራሳች በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ይወሰናሉ፡፡
2. የማህበሩ ዋና ጽ/ቤት በባህርዳር ከተማ ነው፡፡

3. ወደፊት እንደየአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን በሌሎች ቦታዎች በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ሊከፍት ይችላል፡፡
4. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ማህበሩ ስራዎቹን በአግባቡ ያከናውን ዘንድ አስፈላጊ የሆኑ የቁሳቁስና የሰው ሀይል ነገሮች የሚሟሉበትን መንገድ ያመቻቻል፡፡
5. የማህበሩ ጽ/ቤቶች ስራዎች፣ ሀላፊነቶችና አወቃቀር በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ይወሰናሉ፡፡

አንቀጽ 5. የማህበሩ ልዩ አካላት

1. ጠቅላላ ጉባኤው እንደ ኢንስቲትዩት፣ ማዕከል ወዘተ. የመሳሰሉ የማህበሩ ልዩ አካላትን ሊያkቁም እንዲሁም ስራቸውን፣ ሀላፊነታቸውንና አወቃቀራቸውን ሊወስን ይችላል፡፡
2. ልዩ አካላት ተጠሪነታቸው ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 6. የማህበሩ ዓላማዎች**

ማህበሩ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

ሀ/ የመሬት አስተዳደር ባለሞያዎች ሀሳብ በሀገር ደረጃ እንዲወከል ለማድረግ፣ የአባላቱን የሙያ ክብር፣ የሙያዊ ጥቅምና ፍላጐት ማስጠበቅ፤

ለ/ የመሬትን ኢኮናሚያዊ፣ ህጋዊ፣ ማህበራዊና ለአካባቢያ ጥበቃ ያለውን ፋይዳ ለኀብረተሰቡ ማስገንዘብ፣

ሐ/ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን በተመለከተ ለመንግስት የህግና ፓሊሲ ነክ ምክርና ድጋፍ ማድረግ፣

መ/ የመሬት አስተዳደር ባለሞያዎችን ዕውቀትና አቅም ማሳደግ፤

ሠ/ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስልቶችንና ክንውኖችን በሰሚናር፣ ወርኮሾ፣ስምፒዚየም፣ኀትመትና በመሣሰሉት ዘዴዎች ማጐልበት፤

ረ/ የአባላቱን የሙያዊ ስነ ምግባርና ዲስኘሊን መመዘኛዎች ለማቅረብና መጠበቅ፤

ሰ/ በማህበሩ አባላት መካከልና በማኀበሩና በሌሎች ብሔራዊም ሆነ ዓለም አቀፍ መሰል ማኀበራት ጋር ያለውን ግንኙነት ማጐልበት፣

ሸ/ በማኀበሩና በሌሎች ብሔራዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ መሰል ማኀበራት መካከል የሃሳብና የቴክኖሎጂ ልውውጥ ማዳበሪያ መድረክ መፍጠር እና ፣

ቀ/ የተለያዩ የመሬት አስተዳደር ባለሞያዎች በአንድ መድረክ ተሰባስበው ልምድ የሚለዋወጡበትንና የሚደጋገፉበትን መንገድ መቀየስ ናቸው፡፡

**አንቀጽ 7. የማህበሩ አመራር**

ማህበሩ የሚከተሉት የሥራ አመራር አባላት ይኖሩታል፡-

1. ጠቅላላ ጉባኤ
2. ሥራ አስፈፃሚና
3. የቁጥጥር ኮሚቴ

**አንቀጽ 8. የጠቅላላ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር**

ጠቅላላ ጉባኤው የሚከተሉት ስልጣኖችና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

ሀ/ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ከፍተኛው የማህበሩ ስልጣን አካል ነው፡፡

ለ/ የማህበሩን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ይመርጣል፣ ያግዳል፣ያስናብታል፡፡

ሐ/ የማህበሩን የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ይመርጣል፣ ያግዳል፣ ያሰናብታል፡፡

መ/ የማህበሩን ፓሊሲ፣አመታዊ በጀትና የሥራ መርሃ ግብር ያፀድቃል፡፡

ሠ/ በማህበሩ ሌሎች አካላት ስልጣንና ተግባራት ሥር በማይወድቁ ጉዳዩች ላይ ይወሰናል፡፡

ረ/ የማህበሩን መፋረስ ይወስናል፡፡

ሰ/ ይህንን የመተዳደሪያ ደንብ እና የመመሥረቻ ጽሑፍ የማሻሻል ወይም የመሻር ስልጣን የጠቅላላ ጉባኤው ነው፡፡

**አንቀጽ 9. የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎችና ውሳኔዎች**

1. ጠቅላላ ጉባኤው በአመት አንድ ጊዜ ይሰባሰባል፡፡
2. ከጉባኤው አባላት $\frac{1}{2}$ኛ በላይ ከተገኙ ምልዓተ- ጉባኤ ይሆናል፤ ነገር ግን ከሁለት ተከታታይ ጥሪዎች በ|ላ ምልዓተ-ጉባኤው ካልሞላ በተገኙት አባላት ውሳኔዎች መወሰን ይችላሉ፡፡
3. የጉባኤው ውሣኔ በአባላት ድምፅ ብልጫ ይወሰናል፤ ድምጹ ዕኩል ከተከፈለ ሰብሣቢው ያለበት ወገን ወሣኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

**አንቀጽ 10. ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ**

1. ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ፕሬዚዳንት፣ ም/ፕሬዚዳንት፣ ፀሐፊ፣ ገንዘብ ያዥ፣ ሂሣብ ሹምና አንድ ተጨማሪ አባል ይኖሩታል፡፡

2. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በጠቅላላ ጉባኤው በድምፅ ብልጫ ይመረጣሉ፡፡

3. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ዓባላት የሥራ ዘመን 3 ዓመት ይሆናል፤ አንድ የስራ አስፈጻሚ አባል በተከታታይ ከሁለት ጊዜ በላይ መመረጥ አይችልም፡፡

4. የቅርንጫፍ ሀላፊዎች የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 11. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር**

ሀ/ የጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፡፡

ለ/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የጉባኤውን አስቸኳይ ስብሰባ በሰብሣቢው አማካኝነት ይጠራል፡፡

ሐ/ የማህበሩን አመታዊ በጀትና የሥራ ኘሮግራም ለማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ አቅርቦ ያስወስናል፡፡

መ/ አመታዊ የሥራ ክንውንና ሪፓርት ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡

ሠ/ ለሥራ አፈፃፀም የሚረዱ ልዩ ልዩ ንዑሣን ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

ረ/ የማህበሩን ዓርማ ይወስናል፡፡

ሰ/ ሌሎች የማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ  የሚሰጠውን ተግባራት ያከናውናል፡፡

አንቀጽ 12. **የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ስብሰባዎች**

**የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በየዕሩብ ዓመቱ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፤ ሆኖም ፕሬዝዳንቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የአስቸኳይ ጊዜ ስብሰባ መጥራት ይችላል፡፡**

**አንቀጽ 13. ፕሪዚዳንት**

ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው እና ለሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴው ሆኖ የሚከተሉት ስልጣኖችንና ተግባራ ይኖሩታል፡፡

ሀ/ አጠቃላይ የማህበሩን እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፤

ለ/ የማበሩን ጠቅላላ ጉባኤ እና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባዎችን ይመራል፣ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፤

ሐ/ ስለማህበሩ ጠቅላላ የሥራ እንቅስቃሴ ለጉባኤው ሪፓርት ያቀርባል፤

መ/  በሶስተኛ ወገኖቸ ዘንድ ማህበሩን ይወክላል፤

ሠ/ ማህበሩን በመወከል ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ይዋዋላል፤

ረ/ ማህበሩን በመወከል በስብሰባዎች ላይ ይገኛል፣ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎችን በራሱ ተነሳሽነት ወይም በአባላት የፅሁፍ ጥያቄ ይጠራል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፤

ሰ/ የሌሎች የአስፈፃሚ የሥራ አባላትን የስራ አፈፃፀም ይቆጣጠራል፤

ሸ/ አስፈላጊ የሆኑ የወጭ ክፍያዎችን ያዛል፣ ያፀድቃል፤

ቀ/ ከሂሳብ ሹም ጋር  በቼክና በመሰል የባንክ ሒሣብ ማንቀሣቀሻ ሰነዶች ላይ ይፈርማል፤

በ/ በጠቅላላ ጉባዔውና በስራ አስፈጻሚው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 14፡ ም/ፕሪዚዳንት

ም/ፕሬዝዳንቱ ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው እና ለፕሬዝዳንቱ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራታና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ/ የማህበሩን የህትመት ስራዎች በበላይነት ይመራል፡፡

ለ/ ለመፅሔት እና ሌሎች መሰል ዝግጅቶች የማኅበሩ የኢዲቶሪያል ቦርድ ሊቀመንበር በመሆን ይሠራል፤

ሐ/ የማህበሩን የምርምር ስትራተጂ በማዘጋጀት በስራ አስፈጻሚው እንዲጸድቅ ያደርጋል፤

መ/ የፕሬዝዳንቱ ቅርብ ረዳት በመሆን ይሰራል፤

ሠ/ ፕሬዝዳንቱ በሌለበት ጊዜ የማህበሩን ሥራ ይመራል፤

ረ/ የማህበሩን የዓለም ዓቀፍ ጉዳዮች ይቆጣጠራል፤

ሰ/ የማህበሩን የዓለም ዓቀፍ ግንኙነት ስራዎች ዕቅድ ያወጣል፤ ያጸድቃል፤

ሸ/ የማህበሩን የልምድና ቴክኖሎጅ ልውውጥ ያስተባብራል፤

ቀ/ በፕሬዝዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 15፡ ፀሐፊ

1. ፀሐፊው ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው እና ለፕሬዝዳንቱ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ/ ከሊቀ መንበሩ ጋር በመተባበር የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፤ ጥሪውንም ያስተላልፋል፤

ለ/ የማህበሩን መዛግብት ይይዛል፤

ሐ/ በጠቅላላ ጉባኤና በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ ቃለ ጉባኤ ይይዛል፤

መ/ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንና ውሣኔዎችን ለአባላት ያሰራጫል፤

ሠ/ የአባላትን መዝገብ ያዘጋጃል፣ ይያዛል፤

ረ/ ሌሎች በሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ስራዎች ይሰራል።

2. ስራ አስፈጻሚው ጸሀፊው ስራውን በተቀላጠፈ መንገድ እንዲሰራ አስፈላገ የሆነውን የቁሳቁስና የሰው ሀይል ይመድባል።

## አንቀጽ 16. ገንዘብ ያዥ

የገንዘብ ያዥ ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴው እና ለሊቀመንበሩ ሆኖ የሚከተለት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ/ የማህበሩ ገንዘብና ገንዘብ ነክ ሰነዶች አያያዝና ጥበቃ ኃላፊ በመሆን ይሰራል፤

ለ/ የማህበሩ ገንዘብ ተቀባይና ከፋይ በመሆን ይሰራል፤ ገንዘቡን በማኀበሩ የባንክ ሒሣብ በሦስት ቀናት ያስገባል፤

ሐ/ የማበሩን ሂሣብ ከሊቀ መንበሩ ወይም ከም/ሊቀ መንበሩ ጋር በመፈረም ከባንክ ያወጣል፣ ያስገባል።

## አንቀጽ 17. ሂ/ሹም

ሂ/ሹም ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው እና ለሊቀመንበሩ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ/ የማህበሩን ገንዘብ ነክ /የሂሣብ መዛግብትና/ ልዩ ልዩ ሰነዶች ይይዛል፣ ይጠብቃል፤

ለ/ የማህበሩን የገንዘብ አጠቃቀም ስርዓት በሥራ እንዲተረጐም ያደርጋል፤

ሐ/ ለማንኛውም የማህበሩ ወጭ በወጭ ማዘዣ ላይ ይፈርማል፤

መ/ ከፕሬዝዳንቱ ጋር በመሆን በቼክና በመሰል የባንክ ሒሣብ ማንቀሣቀሻ ሰነዶች ላይ ይፈርማል፤

ሠ/ የማህበሩን የገንዘብ አቅም በሚመለከት የሂሣብ ሪፓርቶች ያዘጋጃል፤

ረ/ ከገንዘብ ያዥ ጋር በቅርብ በመሥራት በማህበሩ ቁጥጥር ስር ያለ ገንዘብ በስርዓት እንዲጠበቅ ያደርጋል፤

ሰ/ የማህበሩ ሂሣብ እንቅስቃሴ መሠረታዊ የሂሣብ አያያዝ ዘዴን መሰረት በማድረግ መስራቱን ያረጋግጣል፣ይከታተላል፤

ሸ/ ማንኛውም የማበሩ ንብረት በስርዓት ተመዝግቦ መያዙን ያረጋግጣል፤

ቀ/ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ፣ የወጭ የባንክ ተንቀሣቃሽ ቼክ ይይዛል፤

በ/ ሌሎችንም ከሥራው ጋር ተዛማጅነት ያላቸውና በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡ ተግባራት ያከናውናል፡፡

**አንቀጽ 18. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል**

ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው እና ለሊቀ መንበሩ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ/ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሰባዎች ላይ በመገኘት ይካፈላል፣ ድምፅ ይሰጣል፤

ለ/ ሌሎች ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውና ከሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

**አንቀጽ 19. የኦዲት ኮሚቴ**

1. የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት በጠቅላላ ጉባኤው በድምጽ ብልጫ የሚመረጡ 3/ሶስት/ አባላት ይኖሩታል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ የውስጥ ኦዲተር ይሆናል፡፡
2. የኦዲት ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ነው፡፡
3. የኮሚቴው የአገልግሎት ዘመን ሶስት ዓመት ይሆናል፡፡
4. ኮሚቴው ሊቀ መንበር፣ ፀሐፊ እና አባል ይኖሩታል፡፡
5. የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት በተከታታይ ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጡ አይችሉም፡፡
6. ከኮሚቴው አንድ አባል ቢጉድል ቀሪ አባላት ከማህበሩ አባላት ውስጥ እስከሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባኤ የሚያገለግል አንድ አባል ሊሰይሙ ይችላሉ፤ጉድለቱ ከአንድ በላይ ከሆነ ግን አስቸኳይ ጉባኤ ተጠርቶ ምርጫ ይካሄዳል፡፡

7. የኦዲት ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ሆኖ የሚከተሉት ስልጣኖችና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የማህበሩን የሂሣብ ሰነድ፣ ጥሬ ገንዘብና አጠቃላይ ሀብት የመቆጣጠር እንዲሁም በማንኛውም ጊዜ ሰነዶችን ጠይቆ የማግኘት፣ የመመርመር ስልጣን አለው፤

ለ/ በዓመት ሁለት ጊዜ የማህበሩን የሂሣብ መዛግብት ወይም ወጪና ገቢ ይመረምራል፤

ሐ/ የማህበሩን ደንቦችና መመሪያዎች እንዲሁም የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሣኔዎች በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ለሚመለከታቸውም ግኝቱን ያሣውቃል፤

መ/ ስለማህበሩ የገንዘብ እና የንብረት አያያዝ እንዲሁም አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ በዓመት አንድ ጊዜ ለጠቅላላ ጉባኤ ሪፓርት ያቀርባል፤

**አንቀጽ 20. የማህበሩ አባል ስለመሆን**

1. የማበሩን ዓላማ የሚደግፍና በሕግና በማህበሩ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ሁሉ የማህበሩ አባል መሆን ይችላል።

2. ማህበሩ 5 ዓይነት አባላት ይኖሩታል፤ እነርሱም ሙሉ አባል፣ ተባባሪ አባል፣ ተkማዊ አባል፣ የክብር አባልና የተማሪ አባል ናቸው።

3. የማህበሩ አባል ለመሆን የጽሁፍ ማመልከቻ ማስገባትና ማህበሩ የሚያዘጋጀውን የአባልነት ማመልከቻ ቅፅ መሙላት ያስፈልጋል።

**አንቀጽ 21. የአባልነት መስፈርቶች**

ሀ/ በመሬትአስተዳደር፣ ሲቪል ምህንድስና፣ ጂ አይ ኤስ፣ ጂኦዴሲ፣ የመሬት ዕቅድ፣ ቅየሳ፣ኢኮኖሚክስ፣በሕግ፣በጆግራፊ፣በሀገር ልማት ጥናት በግብርና ወይም ሌሎች ከመሬት ጋር ቅርርብ ባላቸው ሞያዎች የመጀመሪያ ዲግሪና በላይ ያለው፤ወይም

ለ/ ከላይ በተጠቀሱት ዘርፎች ዲኘሎማ ወይም ተመጣጣኝ የት/ት ደረጃ ያለው ሆኖ የ2 ዓመት የሥራ ልምድ ያለው ወይም የሁለት ዓመት የስራ ልምድ ባይኖረውም በመሬት ጉዳይ ላይ ተገቢውን ምርምር ያደረገ ከሆነ፤እና

ሐ/ ማኀበሩ የሚያስቀምጠውን ተጨማሪ መስፈርት የሚያልፍ ከሆነ የማኀበሩ አባል መሆን ይችላል።

መ/ ሆኖም የማህበሩ ምስረታ በዓል ቀናት የተሳተፈ ማንኛውም ግለሰብ መስራችና ሙሉ አባል ይሆናል።

**አንቀጽ 22. የአባላት መብት**

1. ሙሉ አባላት ማህበሩን በተመለከቱ ጉዳዩች ላይ እኩል መብት አላቸው፡፡

2. ሙሉ አባላት የሚከተሉት መብቶች ይኗሯቸዋል፡-

ሀ/ በማንኛወም ጉዳይ ላይ ድምፅ የመስጠት፤

ለ/ በፈለጉ ጊዜ ከማህበሩ የመውጣት /የመሰረዝ/፤

ሐ/ በማህበሩ አሠራር የሥራ አካሄድ ላይ አስተያየት የመስጠት፣ የማቅረብ፤ እና

መ/ በማህበሩ ሰብሳባዎች ላይ የመሣተፍ፣ ሀሣብን የማራመድ፣የመምረጥ እና የመመረጥ፡፡

**አንቀጽ 23. ተባባሪ አባልነት**

1. ከላይ ከተጠቀሱት ዋና አባላት ውጪ የሆኑና

ሀ/ ከተወካዩች ምክር ቤት፣ ከክልል ምክር ቤቶች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚመጡ፣ ወይም

ለ/ በማንኛውም የትምህርት መስክ ቢያንስ ዲፕሎማ ወይም 10+3 የምስክር ወረቀት ያላቸው ሰዎች እና የማህበሩን በጐ አላማ የሚደግፉና የሚያግዙ እና ማህበሩ የሚያስቀምጠውን ተጨማሪ ዝርዝር መስፈርት የሚያሟሉ ተባባሪ አባል መሆን ይችላሉ፤

2. ተባባሪ አባል የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት የለውም/የላትም/፡፡ ሆኖም በምርጫ ወቅት በመገኘት አስተያየትና ሐሣብ የመስጠት እንዲሁም በማህበሩ ስራዎች በንቃት የመሳተፍ መብት ይኖረዋል/ታል፤

አንቀጽ 24. ተkማዊ አባልነት

ማንኛውም ተkም መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆነ፣ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ሀገር፣ ለትርፍ የተkkመም ሆነም አልሆነም የማህበሩን ዓላማዎች እስከደገፈና ማህበሩ የሚያወጣቸውን መስፈርቶች እስከአሟላ ድረስ የማህበሩ ተkማዊ አባል መሆን ይችላል፡፡ ይህም ለአብነት የአበባ ተክል፣ ሪል እስቴትና ቡና ማህበራትን ይጨምራል፡፡

አንቀጽ 25. የተማሪ አባልነት

1. ማንኛውም ተማሪ የማህበሩን ዓላማዎች እስከደገፈና ማህበሩ የሚያወጣቸውን መስፈርቶች እስከአሟላ ድረስ የማህበሩ አባል መሆን ይችላል፡፡
2. አንድ ተማሪ ከተመረቀ በ|ላ ሌሎች መስፈርቶችን እስካሟላ ድረስ ማመልከቻ በማቅረብ በቀጥታ አባል መሆን ይችላል፡፡

አንቀጽ 26. የክብር አባልነት

1. ማንኛውም ሙያዊ ስነ ምግባሩና ብቃቱ የተመሰከረለትና ለማህበሩ ዓላማዎች አፈጻጸም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አስተዋጽኦ ያደረገ ሰው የማህበሩ የክብር አባል መሆን ይችላል፡፡
2. የክብር ዓባላት መዋጮ እንዲከፍሉ አይገደዱም፡፡

**አንቀጽ 27. የአባልነት ግዴታ**

**አባላት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኗሯቸዋል፡**

ሀ/ የማህበሩን የመመሥረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ የማክበር፤

ለ/ ማህበሩን ለማሻሻል ለሚደረገው ጥረት በምርምርም ሆነ በሌላ መንገድ ሁሉ የመሣተፍ፤ እንዲሁም ከፍተኛውን የሙያ ሥነ-ምግባር በመከተል የማኅበሩን ዝናና መልካም ስም የመጠበቅ፤

ሐ/ ማህበሩ በሚያካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ የመሣተፍ፤

መ/ በማህበሩና በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ውሳኔዎች የመገዛት፤ እና

ሠ/ የማህበሩን የመመዝገቢያ ክፍያ እና የአባልነት መዋጮ እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ጉባኤው የሚወስናቸውን ሌሎች ክፍያዎች በወቅቱ የመክፈል ግዴታ ናቸው፡፡

**አንቀፅ 28. የስነስርዓት እርምጃ/ከአባልነት ስለመሰረዝ/**

1. ያለበቂ ምክንያት ለተከታታይ ሦስት/3/ ዓመታዊ ክፍያ ያልከፈለ አባል ምክር አዘል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት የአባልነት ክፍያውን እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

2. ከሦስት /3/ ዓመታት በላይ ያለበቂ ምክንያት መዋጮ ያልከፈለ አባል ውዝፉንና እንደነገሩ ሁኔታ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚወስነውን የገንዘብ መቀጫ እንዲከፍል

ይደረጋል፡፡ ሆኖም አባሉ በዚህ ሣይታረም ለአንድ/1/ ዓመት ክፍያ አቋርጦ ከቆዬ ውዝፉን እንዲከፍል ተደርጎ ከአባልነት እንዲሰረዝ ጥያቄ ቀርቦ በጠቅላላ ጉባኤ ይወሰናል፡፡

3. አባሉ /ሏ/ ከማህበሩ ከመሰረዙ /ዟ/ በፊት ለማህበሩ የከፈለው/ችው ገንዘብ ወይም ቁሣቁስ አይመለስም ወይም ለዚህ ማካካሻ አይሰጥም፡፡

4. አንድ አባል ቢዛወር /ብትዛወር/ በተዛወሩበት ቦታ ቅርንጫፍ ካለ በዚያው በኩል የሚቀጥል/ምትቀጥል ሲሆን ነገር ግን ቅርንጫፍ ከሌለ በአመት አንድ ጊዜ ወይም እንደአመችነቱ ባሉበት ቦታ ሆነው ወርሃዊ ክፍያቸውን መላክ ወይም ገቢ ማድረግ ይችላሉ፡፡

5. አንድ አባል ግዴታውን ካልተወጣ ወይም የማህበሩን ክብር ሊጉዳ የሚችል ሥራ ሠርቶ ሲገኝ በስራ አስፈፃሚ ኮሚተው የሥነ-ሥርዓት እርምጃ እንዲወሰድበት ይደረጋል፡፡

አንቀጽ 29. የአባልነት ፍጻሜ

አንድ አባል ከሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ሲከሰትበት የአባልነቱ መጨረሻ ይሆናል፡-

ሀ. ሞት፣

ለ. የማህበሩ መፍረስ፣

ሐ. የአባልነት ማብቂያ ጥያቄ በጽሁፍ ሲቀርብ፣ እና

መ. የፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም የዲስፕን እርምጃ፡፡

**አንቀጽ 30. የማህበሩ ቅርንጫፎች**

1. ማኀበሩ ተጠያቂነታቸው ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሆነ በየክልሎች ቅርንጫፎች ሊኖሩት ይችላል፡፡ ቅርንጫፎች ለመመስረት ቢያንስ አስር አባላት ሊኖሩ ይገባል፡፡
2. ተጉራባች ክልሎች በድምር ቢያንስ 10 አባላት ይዘው ቅርንጫፎች መክፈት ይችላሉ፡፡
3. ቅርንጫፍ ማኀበራት በስራ አስፈጻሚው የሚሾም ቢያንስ አንድ የቅርንጫፍ ኃላፊ እና ፀሐፊ ይኖራቸዋል፡፡

4. የቅርንጫፍ ሀላፊዎች የስራ አስፈጻሚው አባላት ይሆናሉ፡፡

5. የማህበሩ ቅርንጫፎች የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሯቸዋል፡

ሀ/ አዳዲስ አባላትን ይመርጣሉ፣ የአባላት መዋጮ ሰብስበው ለማኅበሩ ያስተላልፋሉ፤

ለ/ የማኅበሩን ዓላማዎች ለሚወክሉት የክልል መስሪያ ቤቶችና ባለሞያዎች ያስተዋውቃሉ፣ያስፈፅማሉ፤

ሐ/ የቅርንጫፍ ማኅበሩን መመሪያዎችና ደንቦች ያዘጋጃሉ፣ ይህንንም ለዋና ማኅበሩ አቅርበው ያስፀድቃሉ፤

መ/ የክልሉን መሬት ነክ ተጨባጭ ሁኔታዎና ክንውኖች ለዋና ማኅበሩ በዓመት 1 ጊዜ ያቀርባሉ፤

ሠ/ ከስራ አስፈጻሚው የሚሰጣቸውን ሌሎች ስራዎች ያሠራሉ፤

አንቀጽ 31. የገቢ ምንጭና አስተዳደር

1. ከተማሪዎች በስተቀር ለሁሉም አባላት የመመዝገቢያ ክፍያ 40.00 ይሆናል፡፡
2. የአባልነት መዋጮ በዓመት አንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ ለሙሉ አባላት 120.00፣ ለተባባሪ አባላት 60.00፣ ለተkማዊ አባላት 1000.00 እና ለተማሪ አባላት 10.00 ብር ይሆናል፡፡
3. ከላይ የተቀመጠው ቢኖርም የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ወቅታዊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የመዋጮውን መጠን ከማሻሻልና ከመወሰን አይከለከልም፡፡
4. ሌሎች የገቢ ምንጮች፡-

ሀ/ እንደ ማማከር አገልግሎት ያሉ በልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ኘሮግራም የሚገኝ ገንዘብና ቁሣቁስ፤

ለ/ ከበጐ አድራጊ ግለሰቦችና ድርጅቶች የሚገኝ እርዳታ፤

ሐ/ ከመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚገኝ እርዳታ/ስጦታ፤

መ/ የማህበሩን አርማዎች በመሸጥ፣ ከህትመት የሚገኝ ገቢ፣ ከወርክሾፕና ኤግዚብሽን የሚገኝ ገቢ፤

ሠ/ የገቢ ማስገኛ ተቋማትን በማቋቋም የሚገኝ ገቢ፣

ረ/ ከባንክ የሚገኝ ወለድ እና

ሰ/ ሌሎች ህጋዊ የሆኑ የገቢ ምንጮች ናቸው፡፡

5. የማህበሩ ገንዘብ ተቀባይነት ያላቸውን የገንዘብ አያያዝ መርሆዎችና አሰራሮች መሰረት ያደረገ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 32. ማህበሩ የሚቆይበት ጊዜ**

ማህበሩ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

**አንቀጽ 33. ስለማህበሩ መፍረስ**

1. ከማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት $\frac{3}{4}$ኛ ያህሉ ማህበሩ እንዲፈርስ ሲወሰኑ ወይም ማህበሩ እንዳይቀጥል የሚያደርጉ ሕጋዊ ምክንያቶች ሲኖሩ ማህበሩ ይፈርሣል፤
2. ማህበሩ ሲፈርስ ንብረቱ ወይም ሀብቱ ተመሣሣይ ዓላማ ላላቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ወይም በጐ አድራጊ ድርጅቶች ወይም ማህበራት እንዲተላለፍ ይደረጋል፤

**አንቀጽ 34. ስለማህበሩ ደንብ መሻሻል**

1. ደንቡን ለማሻሻል ሲጠየቅ ሀሣቡ በ $\frac{1}{4}$ አባላት ከተደገፈ ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ይታያል፡፡
2. ደንቡን ለማሻሻል የቀረበው የማሻሻያ ሀሳብ ወይም ለመለወጥ የቀረበው ሐሣብ ከግማሽ በላይ የጉባኤው አባላት ከተደገፈ ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 35. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ማህበሩ በሕጋዊ አካል በመመዝገብ ተቀባይነት ካገኘበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡